# ጉዳያችን የመሪ ለውጥ ሳይሆን የስርዓት ነው

(ፍፁም አየነው) Feb 23, 2018

ጉዳያችን የመሪ ለውጥ ሳይሆን የስርዓት ነው!፡፡ማንም በዚህ ስርዓት ቢመራ ስርዓቱ የወለደው ነው እንጂ ህዝብ የመረጠው አይደለም፡፡ገዳያችን የሆነውን ስርዓት የሚመራ የገዳዮቻችን አዛዥ እንጂ መሪያችን አይደለም፡፡
የአማራው ህዝብ ትግል ዘሩን መሰረት ያደረገውን ጅምላ የዘር ፍጅት በማስወገድ ብሎም ፍትህና እኩልነት እንዲሰፍን፤ህዝብ የወደደውና የመረጠውን መሪውን ለመቀበል እንጂ ከወያኔዎች መሀከል እኔ ልምራህ የሚለውን ለመቀበል አይደለም፡፡
አማራው ወገኑንና አገሩን ለማዳን ትጥቁን አጥብቆ መከላከልና ትግሉን በጋራ አስተባብሮ አሸናፊ መሆን ለአማራጭ የማይቀርብ ግዴታው ነዉ።ትዕቢትና ትምክህት የወጠረው የወያኔ ስብስብ በጦር ይደመሰሳል፡፡ክንዶቻችን ሁሉ በጦር መሳሪያችን ላይ ይሁኑ፤ትኩረታችን ትግላችን ላይ ይሁን፡፡

ያልተደራጀ ህዝብ አቅምና ተቀርቋሪ አይኖረውም፣አቅምና ተቀርቋሪ የሌለው ደግሞ በሌሎች ተፅዕኖ ስር መውደቁ አይቀሬ ነው ፡፡በተለይ አማራ በጠላትነት የተፈረጀ እንደ መሆኑ መጠን ከጠላቶቹ የሚደርስበትን ጥቃት በሚገባቸው ቋንቋ ለማናገር በመስማማትና በመደማመጥ የሚጠበቅብንን እናድርግ፡፡ እህል ውኃቸው የተሟጠባቸው ወያኔዎች የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ ሆነው የዳግም የባርነት ቀንበር የአማራ ህዝብ ላይ ለመጫን ከመድረክ ጀርባ በተሰራ የሸፍጥ ፓለቲካቸው የዱላ ቅብብሎሻቸውን ተያይዘውታል፡፡የአማራ ወጣት ከዚህ የቦግ ብልጭ የአራጆች ድራማ ላይ ጆሮህን እና አይንህ ነቅለህ መራራው ትግል ላይ መልስ፡፡ጊዜ ሊገሉበትና ሊያፈዙበት የደረሱት ተውኔት ለመድረክ ሳይደርስ በትግልህ ባለበት ትቋጨዋለህ፡፡

ዛሬም እንላለን ትግላችን የአማራ ህዝብ እየደረሰበት ካለው ልዩ የሆነ የፓለቲካ፣የኢኮኖሚ፣የማህበራዊ፣የስነ-ልቦናና የዘር ጥቃት ነፃ ወጥቶ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባትና ለዚህም የሚቆሙ ነፃና ገለልተኛ የዴሞክራሲ ተቋማት ዕውን የሚሆኑባት፤የኢትዮጵያ ህዝብ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት የተረጋገጠባት፤የህዝብ አንድነት፤ፍቅርና እኩልነት የጠነከረባት፤ጠንካራና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕውን ሆና ማየት።ለዚህም የማንከፍለው መስዋዕትነት የማናፈሰው ደም አይኖርም፡፡

በቁርጥ ቀን ልጆች አጥንትና ደም ወያኔ ይደመሰሳል! አማራው ከታወጀበት የዘር ማጥፋትና ማፅዳት እራሱን ይታደጋል!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!


አዴኃን